**13 ኛ ዓመት ቁጥር 6**
**13th Year No 6**

ባህር ዳር መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State

<u>ማውጫ</u>

<u>አዋጅ ቁጥር **153/2000** ዓ.ም</u>
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስተ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አወጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ

## in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.95
Unit price ------

<u>አዋጅ ቁጥር **153/2000** ዓ.ም</u>

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አወጅ

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት ሲኖርበት ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 67/2/ሐ ሥር በመደንገጉ፤

የሰበር ችሎት አቋቋሞ የአሠራር ሥርዓቱን መወሰን የተቀላጠፈ ፍትህን ለማስፈንና

ተደራሽነቱንም ለማረጋገጥ እንደሚጠቅም በመታመኑ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቅጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጀል።

**1.** <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገ ለማሻሻል የወጣ አወጅ ቁጥር 153/2000 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2.** <u>ማሻሻያ</u>

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 11/1998/ እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

ሀ/ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 8 የገባ ሲሆን በዚህ የተነሣ የአዋጁ አንቀጽ 8 አንቀጽ 9 ሆኖ ተስተካክሏል፣ ቀሪዎቹም የአዋጁ ተከታታይ አንቀጾች በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት ተሸጋሽገዋል፡፡

**1.** <u>ስለ ሰበር ችሎት</u>

1. በጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድን ጉዳይ ከአምስት የማያንሱ ዳኞች የሚሰየሙበት የሰበር ችሎት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለባቸው በሚከተሉት የክልል ጉዳዮች በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ/በወረዳ ፍርድ ቤት ተወስነው በይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለቁ ጉዳዮች ፣ እና

ለ/ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስነው በይግባኝ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለቁ ጉዳዮች ።

3. በሰበር እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ የሚከተሉትን ሥርዓቶች ሊያሟላ ይገባል፡-

ሀ/አቤቱታ የሚያቀርበው ተከራካሪ ወገን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በአቤቱታው ላይ በዝርዝር ማቅረብ ይኖርበታል ።

ለ/ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔና የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሣኔ ግልባጭ ከሰበር አቤቱታው ጋር ማያያዝ አለበት።

4. የሰበር አቤቱታ የሚቀርበው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ካገኘበት ጀምሮ በ 60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነው ።

5. በዚህ አንቅጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም አበቱታ አቅራቢው አቤቱታውን በውቅቱ ያላቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ አቤቱታውን ለማቅረብ የማስፈቀጃ ፋይል መክፈትና ከተፈቀደለትም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ በተቀመጠው ሥራዓት መሠረት አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል።

6. የሰበር ችሎቱ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ ለማጽናት፣ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ይችላል ።

**3.** <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ በክልሉ መንግሥት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

መጋቢት **15** ቀን **2000** ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት